## 5/ ለአደጋ ተጋላጭነት:

በግሪክ ህገስርአት መሰረት የለአደጋ ተጋላጭነት እሚያስብሉት እነዚህ የሚከተሉት ናቸው፡

ተንከባካቢ የሌላቸው ለአቅመ አዳም/ሄዋን ያልደረሱ ፡ አካል ስንኩሎች ፣ፈውስ በሌለው በሽታ የሚሰቃዩ ፣ወይም ከባድ የጤና ችግር ያለባቸው፡
- ሽማግሌዎች/አሮጊቶች (እድሚያቸው ከ65በለይ)
- እርጉዞች ወይ ደሞ በቅርብ ግዜ የወለውዱ
- አንድ ወላጅ (አባት /እናት )ብቻውን ከህጻናት ልጆች ጋር
- የስቃይ ሰለባ የሆኑ፣የተደፈሩ፣ሌላም አይነት አካላዊ፣ስነልቦናዊ፣ወሲባዊ ጥቃት፣ብዝበዛ ፣በጭንቀት የተነሳ የሚፈጠር ያለመረጋጋት(ስትረስ)እንዲሁም በጉዞ ቤተሰቦቻቸው ባህር ላይ አደጋ ደርሶባቸወ የተረፉ፡
- የሰው ንግድ ሰለባ የሆኑ፡

የለአደጋ ተጋላጭነት ለማረጋገጥ ግምገማ ያደርጋሉ፡
- የጤና ምርመራ_ በግሪክ ባለስልጣኖች የቀጠሮ ፕሮግራም ይያዝልዎታል፡
- ካስፈለገም የስነልቦናግምገማ ̇_የስነልቦና ባለሞያ ጋር መነጋገር ከፈለጉ የጤና ምርመራ በሚያደርጉበት ሰአት ለየጤና ባለሞያ ሰራተኞው ማሳወቅ ይችላሉ፡ በመቀጥለው ግዜ ከየስነልቦና ባለሞያ ጋር በግሪክ ባለስልጣኖች የቀጠሮ ፕሮግራም ይያዝልዎታል፡

ከግምገማው በህዋላ እርስዎ ለአደጋ ተጋላጭ መሆንዎን ከታመነበት እሚቀጥለው ሂደት ይሆናል ማለትም:
- የጆግራፊያዊ ክልል እገዳ የተደረገብዎት ይነሳልዎታል ይህም ማለት ከፈለጎ ከሌስቮ መሄድ ይችላሉ፡
- ያደረጉት ግምገማ የጥገኝነት ጥያቄ ላይ መሰረት ይኖረዋልማለትም ለምን ካገርዎ እንደወጡና ወደ አገርዎ መመለስ እንደማይፈልጉ ፡ስለዚህም ቱርክ ቢመለሱ በደህንነት መኖር እንደማይችሉና ቱርክ ውስጥ የአለም አቀፍ ጥገኝነት የማግኘትእድሉ እንደሌሎት ማረጋገጫ ማቅረብ አያስፈልግዎትም፡፡

ማስታወስ ያለብዎት የለአደጋ ተጋላጭነት ለማረጋገጥ በሚደረገው ግምገማና በቃለመጠይቅዎ ወቅት ማንኛውም እሚሰጡን መረጃዎች ሚስጢራውነታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

ማስታወስ ያለብዎት የለአደጋ ተጋላጭነትዎን የሚያረጋግጡ እያንዳንዱንነገሮች በተቻለዎት መጠነ ቶሎ በወቅቱ በግልጽና በሙሉነት ባለው መንገድ ማሳወቅ ይኖርቦታል፡ሆኖም ግን በየለአደጋ ተጋላጭነት ለማረጋገጥ በሚደረገው ግምገማ ላይ ካላሳወቁ ቆይተውም ማሳወቅ ይችላሉ፡በተጨማሪም በቃለመጠይቅ ወቅት ለአደጋ ተጋላጭነትዎን የማሳወቅ እድል አለዎት፡፡

ማስታወስ ያለብዎት የለአደጋ ተጋላጭነትዎ እውቅና ማግኛት ማለት የአለም አቀፍ ጥገኝነት እውቅና ጋር አንድ አይደለም እርስዎ ለአደጋ ተጋላጭነትዎ እውቅና ስላገኙ በቀጥታ የአለም አቀፍ ጥገኝነት እውቅና አገኙ ማለት አይደለም፡ሁለቱ የተለያየ ትርጉም ነው ያላቸው፡ስለዚህ ለጥገኝነት ጥያቄዎ ቃለመጠይቅ ቅድመዝግጅት ማድረግና በቀነቀጠረዎ መገኛት ይኖርቦታል፡፡

## 6/ የጥገኝነት ማመልከቻ ምዝገባ:

ምዝገባውን ለማድረግ በ የጥገኝነት መስራቤት መገኘት ይኖርቦታል፡በዚህ ቀን የጉዳይዎ ቁጥር (ኬዝ ነምበር)፣የጥገኝነት ጠያቂ ካርድ፣የቃለመጠይቅ ቀነቀጠሮ ይሰጥዎታል፡፡

በግሪክ የጥገኝነት መስራቤት ሰራተኞች ወይም በግሪክ ፖሊሶች የጣት አሻራዎ ይነሳል ፡፡

አጠር ባለ መልኩ የትውልድ አገርዎን ለምን ጥለው ለመውጣት እንደተገደዱ ይጠየቃሉ፡

የቤተሰብ መሰባሰብ:
- ማስታወስ ያለብዎት ሌላ የአውሮፓ አገር ውስጥ ባጣም ቅርብ የሆነ የቤተሰብ አባል ካለና ከሱ ጋር መሰባሰብ እሚፈልጉ ከሆነ በምዝገባው ወቅት መንገር ይኖርቦታል፡ ፡ለምሳሌ ከባለቤትዎ ጋር፣ለአቅመ አዳም/ሄዋን ካልደረሱ ልጆችዎ ጋር፣እንዲሁም ማንኛውም ዘመድዎ የሆነ እራሱን የማይችልና የእርስዎ እርዳታ የሚያስፈልገው ከሆነ ፣ማመልከት ይችላሉ ፡፡ ይህ የቤተሰብ መሰባሰብ ማመልከቻ በምዝገባ ወቅት ካላቀረቡ ከምዝገባ በህዋላ በአጭር ግዜ ማቅረብ ይኖርቦታል፡፡ግዜው ከረዘመ የሚመጣ መንገላታት ስለአለ፡
- ሌላ የአውሮፓ አገር ውስጥ ጋር መሰባሰብ ከሚፈልጉት የቤተሰብ አባል ከሚኖርበት አገር ውስጥ ያለውን ማንኛውም የማስረጃ ሰነዶች ማስገባት ይኖርቦታል(ለምሳሌ መኖርያ ፍቃድ ፣የሚኖርበት አድራሻ )እንዲሁም የቤተሰብ አባላት መሆናችሁን የሚያረገግጥ ሰነዶች ማቅረብ አለብዎት፡፡
- ማስታወስ ያለብዎት የመሰባሰብ ማመልከቻ ከ የቤተሰብ አባል ጋር ሲያደርጉ በጽሁፍና በፎርማ ማስገባት ይኖርቦታል_ በምዝገባው ወቅት እርስዎ መሰባሰብ እንደሚፈልጉ ብቻ በመግለጽ ማመልከቻዎ ብቃት አይኖረውም፡፡
- የቤተሰብ መሰባሰብ ማመልከቻ (ማለትም በጽሁፍና በፎርማ የተደገፈ ማመልከቻ)የጊዜ ገደብ አለው ፡የጥገኝነት ማመልከቻ ምዝገባ ካደረጉበት ቀን ጀምሮ እስከ 3ወር ውስጥ ድረስ ብቻ ነው ማመልከት የሚችሉት፡ግን የቤተሰብ አባልዎ ጀርመን አገር እሚገኝ ከሆነ የቤተሰብ መሰባሰብ ማመልከቻ ማስገባት እሚችሉት ሌስቮ ከደረሱበት ቀን ጀምሮ እስከ 3ወር ውስጥ ድረስ ብቻ ነው፡

ማስታወስ ያለብዎት የምታቀርብዋቸው የሰነዶች ግልባጭ ትክክለኛ መሆን አለባቸው ስም ወዘተ ምክንያቱም የማመልከቻው ምዝገባ ትክክል እንዲሆን፡፡

ማንኛውም ያቀረባችሁትን የግል ሰነዶች የመስያቤቱ ሰራተኛች ይመልሱላችሁዋል ፓስፖርት ከሆነ እሚመለከተው አካል ይይዘዋል፡፡

ማስታወስ ያለብዎት በምዝገባ ወቅት ትክክለኛ ስምዎንና ማንነትዎን ማስመዝገብ ይኖርቦታል(ስም የትውልድ ቀን ወዘተ)ምክንያቱም ከምዝገባ በህዋላ ማስተካከል አይቻልም፡ ማስታካከል እሚችሉት ኦርጂናል ፓስፖርት ወይ መታወቅያ ካልዎትና በዚህ ማረጋገጥ ከቻሉ ብቻ ነው፡፡

በምዝገባው ወቅት በጥንቃቄ ማስታወስ ያለብዎት የምዝገባው መጨረሻ ላይ የማረጋገጥ ሂደት ይካሄዳል(ማለትም የሰጡት መረጃዎች በሙሉ ፎርሙ ላይ ትክክል መሆኑን ያረጋግጣሉ)ካዩት በህዋላ ስህተት ካለው ለመዝጋቢው ስህተቱን መንገር አለብዎት፡፡

## 7/ የጥገኝነት ቃለመጠይቅ:

ቃለመጠይቅን በተመለከተ:
- የቃለመጠይቅዎ ቀነቀጠሮ በተሰጠዎት የጥገኝነት ጠያቂ ካርድ ላይ ተመዝግቦዋል
- ቃለመጠይቅዎ የሚደረገው በሞርያ አይደለም በፓያኒነው ከሞርያ ወደ ፓያል በአውቶቡስ ይ መጣሉ ፡፡
- ማስታወስ ያለብዎት ሁሉንም የህክምና ሰነድዎትን ማቅረብና ያለብዎትን የጤና ችግር ማብራራት ይኖርቦታል (ያንን ቀንና ከዛም በፊት የሚሰማዎን ስሜት) ለአደጋ ተጋላጭነትዎን ለማስረዳት ዕድሉ ስላሎት በዝርዝርና በሙሉነትለመግለጽ ይሞክሩ ፡፡
- የጉዳይዎን ሃላፊነት ለያዘው ጠያቂ የ ለአደጋ ተጋላጭነት ግምገማ እንዳላደረጉ ማስረዳት ይኖርቦትዋል፡፡
- የጉዳይዎን ሃላፊነት ለያዘው ጠያቂ የቅርብ ጊዜ የስነልቦና ሁኔታዎን ወይ በእንጥልጥል ላይ የሉትን ማንኛውም የህክምና ቀጠሮ በተመለከተ ያሉት ን ወረቀቶች ማሳየት እንዳለብዎት ማስታወስ ይኖር ቦታል
- ማስታወስ ያለብዎት ይህ ወቅት ጉዳይዎን በተመለከተ በዝርዝር በእርግጠኛነት ሁሉንም ነገሮች ለማስረዳት እምትችሉበት ትልቅአጋጣሚና እድል ነው በተለይ በሰነዳዊ ኦርጂናል መልኩ (ስእሎች፣Fascebook ላይ ያሉ ልጥፎች ፣ጋዜጣ ላይ የወጡ ጽሁፎች፣የስራዎ መታወቅያ፣(የወጡበት ምክን ያት ከስራዎ ጋር ግ ንኙነት ካለው )ከቃለመጠይቁ በህዋላ ተጨማሪ ማረጋገጫ ሰነዶች ማስገባት ይችላሉ ፡፡ ተጨማሪ ማረጋገጫ ሰነዶች ማስገባት የሚችሉት የጊዜ ገደብ ቃለመጠየቁንካደረጉ በህዋላ በአምስት ቀን ውስጥ መሆን አለበት ፡፡ ግ ን ከዚህ የጊዜ ገደብ በህውላ ካስገቡ ምናልባት ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል ፡፡

እሚትጠየቁት ጥያቄዎች
- የግልዎን ማንነትዎን ስም ውዘተ
- የጤና ሁኔታዎ/ ለአደጋ ተጋላጭነትዎ
- ዜግ ነትዎ ሁኔታና ከለአደጋ ተጋላጭነትዎ ጋር በማዛመድ ቱርክ ለእርስዎ ዋስትና ያላት አገር እንደሆነችና እዛ ቢመለሱ የአለም አቀፍ ጥገኝነት የምገኘት እድ ል እንዳለዎት
- ከአገርዎ የወጡበትን ምክን ያትና ወደ አገርዎ መመለስ እማይችሉበትን ምክን ያት ለምሳሌ ለምን የግድ መውጣት እንዳስፈለጎትና ከተመለሱ ምን ሊያጋጥሞት እንደሚችል እንዲሁም አገርዎ ውስጥ ሌላ አካባቢ በዋስትና መኖርይችላሉ?

እሚከተሉት መብቶች ይኖርዎታል
- በቃለመጠይቁ ወቅት ጠበቃዎን ይዘው መቅረብ ይችላሉ
- ለቃለመጠይቅዎ ለመዘጋጀት ግዜ የማግኘት መብት አለዎት ለአደጋ ተጋላጭ ከሆኑ ሰባት ቀን ካልሆኑ አንድ ቀን ይገባዎታል ፡፡ ቃለመጠይቅዎ ቀኑ ከደረሰ ወይም ቀነቀጠሮው በጣም ቅርብ ከሆነ ይህ መብት በጣም አስፈላጊ ነው
- የሚያስተረጉምሎት አስተርጉዋሚ ላይ የብቃት ጥርጣሬ ካለዎት እንዲቀየርሎት የመጠየቅ መብት አእለዎት

- የጉዳይዎን ሃላፊነት የያዘው ጠያቂና እንዲሁም አስተርጉዋሚ ጾታ መምረጥ ይችላሉ
- ቃለመጠይቅዎ በእናት ቈንቋዎ የማድረግ መብት አእለዎት፡፡
- ቃለመጠይቅዎ ቀን እንዲተላለፍሎት መጠየቅ ይችላሉ (ከዚህ በፊት ጠይቀው ካልሆነ በቀጥታ ይፈቀድሎታል ግ ን ከዚህ በፊት ጠይቀው ከነበረ በቂ ምክኛት ማቅረብ አለብዎት (ለምሳሌ በከባድ የጤና ችግር ምክንያትቃለመጠይቁን መሳተፍ ወይ መገኘት እንዳልቻሉ ለእንደዚህ አይነት አጋጣሚ ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርቦታል (የሃኪም የጤናዎ ጽሁፍ )ይህ በጣም አስፈላጊ ነው ፡፡
- እረፍት የመጠየቅ መብት አለዎት
- ቃለመጠይቅዎን በመቅረጫው የተቀረጸውን ግልባጭ የመጠየቅ መብት አለዎት ፡፡

እሚከተሉት ግዴታዎች ይኖርዎታል
- በቃለመጠይቅዎ ቀነቀጠሮ የግድ በቅረብ አለብዎት በቃለመጠይቅዎ ቀነቀጠሮ ካልተገኙ ያልመጡበት በቂ ምክንያት ካላቀረቡ ጉዳይዎ ይዘጋል እንደገና አዲስ ጉዳይ ለመክፈትና ለመጀመር በጣም ከባድ ነው ፡፡

## 8/ ይ ግባይ:

መረጃዎች
- ያቀረቡት የጥገኝነት ማመልከቻ ከቃለመጠይቅዎ በህዋላ ውጤቱ አሉታዊ ከሆነ (ተቀባይነት ካላገኘ) ይግባይ የመጠየቅ መብት አለዎት ፡፡
- የይግባይ የጊዜ ገደብ እርስዎ ለአደጋ ተጋላጭነት ግምገማ ያደረጉ ከሆነና ለአደጋ ተጋላ ጭ ከሆኑ በ30ቀን ውስጥ ካልሆኑ በ5ቀን ውስጥ የይግባይ ማመልከቻ ማስገባት አለብዎት ፡፡
- የይገባይ ሂደት የሚፈጸመው በጽሁፍ ነው ፡፡ በጽሁፍ የቀረበው የይግባይ ማመልከቻ አቴንስ በሚገኘው የይግባይ ኮሚቴ ይጠናል፡፡ ኮሚቴው ካልጠራዎት የ እርስዎ መገኘት አያስፈልግም ይህም ማለትለሌላ ቃለመጠይቅ አይቀርቡም ፡፡

መብቶች
- የህግ አማካሪ የማግኘት መብት አለዎት ከመንግስት አንድ ግሪካዊ ጠበቃ በጽሁፍ የሚቀርብ የይግባይ ማመልከቻ ያለምንም ክፍያ ያዘጋጅሎታል፡፡ ይህ ድጋፋዊ ጽሁፍ የእርስዎን ጉዳይና ለምን የአለም አቀፍ ጥገኝነት እንደሚገባዎት የሚገልጽ ሲሆን ይህንን ጽሁፍ ማስገባት እሚቻለው በጣም ከቆየ ጉዳይዎ ከሚታይበት ቀን 2ቀን በፊት መሆን አለበት፡፡የይግባይ ማመልከቻዎን ሲያስገቡ ማመልከቻውን የሚመዘግብ የጥገኝነት መስሪያቤት ሰራተኛ የህግ አማካሪ እንደሚፈልጉ መንገር አለብዎት ፡፡
- የህግ አማካሪ ካልተሰጥዎት ጉዳይዎ የሚታይበት ቀን እንዲራዘም የመጠየቅ መብት አለዎት (ይህም ቢሆን የይግባይ ኮሚቴው ያቀረቡትን የቀን መራዘም ማመልከቻዎን የመቀበል ግዴታ የለውም ጉዳይዎን የህግ አማካሪ ወይም የህግተወካይ ሳይኖርዎትም ጉዳይዎን መመርመር ይችላል፡፡

ማስታወስ ያለብዎት
- ለጥገኝነት መስሪያቤት ወይ ለጠበቃዎ በተለይ ከቃለመጠይቅዎና ከውሳኔ በህዋላ የተሰጠዎትን ማንኛውም የህክምና ሰነዶች ማቅረብ ይኖርቦታል ፡፡
- ከጉዳይዎ ጋር ግ ንኙነት ያላቸውን ማንኛውም ሰነዶች ለጠበቃዎ የይግባይ ጉዳይዎ ከሚታይበት ቀን በጣም በፊት ማቅረብ አለብዎት ፡፡

## 9/ የይግባይ ማመልከቻዎ ውሳኔ አሉታዊ ከሆነ:

የይግባይ ማመልከቻዎ ውሳኔ አሉታዊ ከሆነ ወደ ማረፍያ ቤት መሄድና ወደ ቱርክ ወይም ወደ ትውልድ አገርዎ መመለስ ይችላሉ፡፡ ይህም ሲሆን የአደጋ ተጋላጭ መሆንዎንና ያለመሆንዎ ግምትውስጥ ይገባል፡፡

ህጋዊ የሆኑ አማራጮች _እርስዎና ጠበቃዎ በግል በመገናኘት ስለ ጉዳይዎ ግምገማ ያድርጉ ፡፡
- ፍርድቤታዊ ሂደት _የይ ግባይዎ አሉታዊ ውሳኔ ከተሰጥዎትበመጀመር በ60 ቀን ውስጥ ወደ የግሪክ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት በመሄድ የተወሰነውውሳኔ እንዲሰረዝማመልከቻማስገባትይችላሉ፡፡ይህንንለማድረግ የህግ አማካሪ ድጋፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (NGO) መጠየቅ (የተወሰነ አቅም አስተዳደራዊ አስፈላጊነገሮችን እንዲያግዝዎት) ወይንም የግል ጠበቃዎን በመጠቀም ማድረግ ይችላሉ ፡፡ ሁለተኛውአማራጭ ወጪ የሚያስወጣ ሲሆን ዝርዝሩን የምትይዙት ጠበቃ ሊያብራራልዎት ይችላል፡፡
- እንደገና የሚጀመር የጥገኝነት ማመልከቻ _ከ60 ቀን የይ ግባይዎአሉታዊ ውሳኔ ከተሰጥዎት በህዋላ እንደገና የሚጀመር የጥገኝነት ማመልከቻ የማመልከትመብት አለዎት ፡፡ ማመልከቻዎ አዲስና አስፈላጊ አዲስ ነገር ከጥያቄዎ ጋር የሚያያዝ እንዳለው ለማየት ነው ፡፡ (ለመሳሌ ስለሚኖሩበት አካባቢ ስለ ትውልድ አገርዎ ወይም ከዚህ በፊትስለሚኖሩበት አገር በተመለከተ አዲስ መረጃዎች ፣አዲስ ተጨባጭ መረጃዎች ፣ አዲስ የህክምናሰነዶች ከጉዳይዎ ጋር የሚያያዝ (ለምሳሌ የጥቃት ሰለባ መሆንዎን የሚያረጋግጥሰነድ(ሰርተፊኬት)